መልእክት አምስት

**ለቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ**
**ሕይወታዊ አካል መገንባት**
**ተፈጥሮአዊ ችሎታ ከሕይወት ብስለት ከሆነው**
**የትንሣኤ ችሎታ በተጻራሪ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ነገ. 3፡1፤ 11፡1-8፤ ኢያ. 9፡14፤
1 ቆሮ. 1፡24፣ 30፤ ኢሳ. 45፡15፤ 37፡31፤ ማቴ. 6፡6

**I. ሰሎሞን የጥበብ ሰው እና የእውቀት ሰው ሆነ (2 ዜና. 1፡10፤ ተዛ. ቆላ. 2፡2-3)፤ ሆኖም ግን፣ ብዙ አሕዛብ ሴቶችን ስለወሰደና ጣዖቶቻቸውን ስላመለከ፣ ለሕዝቡም ጣኦታትን የሚያመልኩበትን ስፍራ ስለሠራ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ጥበብ እና ከእግዚአብሔር የተሰጠውን እውቀት አጣ፤ በጣም ሞኝ ሆነ፣ ለመንግሥቱም ጥፋትን አመጣ (1 ነገ. 3፡1፤ 11፡1-8)፦**

*ሀ.* እንደ እግዚአብሔር ልብ የነበረው የሰሎሞን አባት ዳዊት በዚሁ የሥጋ ምኞትን በማርካት ጉልህ እና አስቀያሚ ኃጢአት ወድቋል (2 ሳሙ. 11)፤ በዚህ ሰይጣናዊ ፈተና የሰሎሞን ውድቀት ከአባቱ ይልቅ የሚበልጥ ነበር፤ ውድቀቱ ብዙ እንግዶች ሴቶችን በመውደድ የሥጋ ምኞቱን በማርካት (1 ነገ. 11፡1-3)፣ ሁለት ጊዜ የተገለጠለትን እግዚአብሔርን በመተው (ቁ. 9) እና ይወዳቸው በነበሩት እንግዶች ሴቶች በመማረክ የአሕዛብ ጣዖታትን በማምለክ (ቁ. 4-8) ነበር።

ለ. ሰሎሞን ሰባት መቶ ሚስቶች እና ሦስት መቶ ቁባቶች ነበሩት (ቁ. 3)፤ ፍላጎታቸውን ለማርካት፣ መስገጃዎችን ሠራ፤ ሚስቶቹ "ሌሎችን አማልክት ይከተል ዘንድ ልቡን አዘነበሉት" (ቁ. 4)፤ "ሰሎሞንም የሲዶናውያንን አምላክ አስታሮትን፥ የአሞናውያንንም ርኵሰት ሚልኮምን፥ ተከተለ" (ቁ. 5)።

ሐ. "በዚያን ጊዜም ሰሎሞን ለሞዓብ ርኵሰት ለካሞሽ፥ ለአሞንም ልጆች ርኵሰት ለሞሎክ በኢየሩሳሌም ፊት ለፊት ባለው ተራራ ላይ መስገጃ ሠራ"—ቁ. 7፦

1. ሰሎሞን በሚገዛበት ጊዜ መቅደሱ በኢየሩሳሌም ተገንብቶ ነበር፣ የጌታም ክብር መቅደሱን ሞላው፤ የመቅደሱ ግንባታ ዘመን በእስራኤል ልጆች ታሪክ ውስጥ ወርቃማ ጊዜ ነበር—8፡10-11።
2. ልዩና ብቸኛው ስፍራ ኢየሩሳሌም አንድነትን የሚያመለክት ሲሆን፣ መስገጃዎቹ ክፍፍልን ያመለክታሉ፤ ሁሉም የክፋት አይነት እና አስጸያፊ ነገሮች መስገጃዎችን ከማቆም ጋር የተገናኙ እንደሆኑ እንዲሁ፣ በአዲስ ኪዳን ቃላት፣ ሁሉም አይነት ክፋት ከክፍፍል ጋር የተገናኘ ነው—1 ቆሮ. 1፡10 እና የግርጌ ማስታወሻ 3።
3. በእግዚአብሔር መሻት መሠረት በእግዚአብሔር ሕዝብ የአንድነት መቆሚያ ስፍራ ላይ መቅደሱን የገነባው ሰሎሞን በድጋሚ መስገጃዎቹን ለመሥራት ቅድሚያውን መውሰዱ የሚያስደንቅ ነው—1 ነገ. 11፡6-8።

መ. ይህ ዘሮቹ ከመንግሥታቸው ከዘጠና በመቶ በላይ እንዲያጡ አደረጋቸው፣ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብም በመካከላቸው ለብዙ ትውልዶች በክፍፍል እና ግራ በመጋባት መከራ እንዲቀበሉ አደረጋቸው፤ በመጨረሻም፣ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ምድር አጡ፣ ጣዖት በሚያመልኩ እንግዳ ምድሮች ምርኮኞችም ሆኑ።

ሠ. የእስራኤል አገር አሁንም ድረስ መከራ እየተቀበሉ ያሉት ከሰሎሞን ውድቀት የተነሣ ነው፤ ይህ ለእኛ ምን አይነት ማስጠንቀቂያ እና ማንቂያ ሊሆንልን ይገባል! መጠንቀቅ አለብን፤ የሥጋን ምኞት ለማርካት የሆነ ትንሽ ውድቀት እንኳን የቤተ ክርስቲያን ሕይወትን ሊጎዳ እና የቤተ ክርስቲያንን ግሩም ገጽታዎች ሊገድል ይችላል።

ረ. ስለዚህ፣ እጅግ ትንሽ በሆነው ነገር እንኳን መጠንቀቅ አለብን፤ በሁሉም ነገር በመንፈስ መሠረት መመላለስ አለብን (ሮሜ 8፡4፤ ተዛ. ዘካ. 4፡8-10)፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ በእርሱ ላይ በመደገፍ እና ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን ከእርሱ ጋር አብረው መኖር አለባቸው (ኢያ. 9፡14፤ 2 ቆሮ. 6፡1፤ 1 ቆሮ. 3፡9፤ ማቴ. 1፡23)።

ሰ. የሰሎሞን አሟሟት በሃዘንና በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ነበር (1 ነገ. 11፡40-43)፤ ክብሩ እንደ ሣር አበባ ረገፈ (ማቴ. 6፡29፤ 1 ጴጥ. 1፡24)፣ ግሩሙ ሥራውም እንደሰበከው "የከንቱ ከንቱ" ሆነ (መክ. 1፡2)።

**II. የሰሎሞንን ውድቀት በመንፈሳዊ ሕይወት ብርሃን ሥር ማየት ያስፈልገናል፦**

*ሀ.* ሰሎሞን ጠቢብ ሰው እንጂ መንፈሳዊ ሰው አልነበረም፤ የብቃት ሰው እንጂ የሕይወት ሰው አልነበረም፤ በእግዚአብሔር የተሰጠው የመልካሚቱ ምድር ድሰታው ከፍተኛው ደረጃ የደረሰው በእግዚአብሔር በተሰጠው ስጦታ ነበር፤ ሆኖም ግን፣ በመንፈሳዊ ሕይወት በነበረው አነስተኛ የብስለት መጠን፣ ሥጋዊ ምኞቱን ለማርካት ከነበረው ያልተገራ ፍላጎት የተነሣ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ካለው ከመልካሚቱ ምድር ድሰታ ተቆረጠ—1 ቆሮ. 2፡14-15፤ 3፡1፣ 3።

ለ. በእግዚአብሔር የተሰጠው የሰሎሞን ጥበብ በዘመኑ በዓለም ታላቅ አድርጎት ነበር፤ ሆኖም ግን፣ ጥበቡ ሙሉ በሙሉ ምንም መንፈሳዊ ንጥረ-ነገር በሌለበት በቁሳዊው ክልል ነበር፤ ጥበቡ ሊመጣ ያለው እውነተኛ ጥበብ ጥላ ነበር፣ ሙሉ በሙሉ ከጳውሎስ ጥበብ የተለየ ነበር—1፡24፣ 30።

ሐ. የጳውሎስ ጥበብ ክርስቶስ በልባችን ቤቱን መሥራቱን (ኤፌ. 3፡17)፣ ምልልሳችንን እና ማንነታችንን በመንፈስ መሠረት ማድረጋችንን (ሮሜ 8፡4) እና ሁለቱ መንፈሶች—መለኮታዊው መንፈስ እና የሰው መንፈስ—እንደ አንድ መንፈስ በአንድ ላይ መዋሐዳቸውን (ቁ. 16፤ 1 ቆሮ. 6፡17) በተመለከተ መንፈሳዊ ጥበብ ነበር።

መ. የእግዚአብሔር ምሥጢሮች የተገለጡት በዋናነት ለጳውሎስ ነበር (ቆላ. 2፡2፤ ኤፌ. 3፡3-5፣ 9-10)፤ ዛሬ፣ በአጽናፍ-ዓለም ያለውን ከፍተኛውን ጥበብ ለማወቅ ከወደድን፣ ወደ ጳውሎስ መልእክቶች እውነቶች ንጥር ውስጥ መግባት አለብን፤ እውነተኛው ጥበብ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለማድረግ እና ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወት እና በባሕርይ እኛን እግዚአብሔር ለማድረግ በውስጣችን ለመሆን ጥበባችን በሆነው በክርስቶስ አካል የለበሰው እግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህ፣ የማይወሰን ጥበቡን እና መለኮታዊ ንድፉን የምናሳይ የሦስታንዱ አምላክ ድንቅ የጥበብ ሥራ፣ ግጥም እንሆናለን (1 ቆሮ. 1፡24፣ 30፤ ኤፌ. 2፡10፤ 3፡9-11)።

**III. ሰሎሞን በተፈጥሮአዊ ችሎታ የተሞላ ሰው እንጂ የሕይወት ሰው፣ ጥበቡ ስጦታ እንጂ የሕይወት መጠን ያልሆነ ሰው ነበር፤ ያከናወናቸው ሥራዎች በእግዚአብሔር ከተሰጠው የጥበብ ስጦታ የመጡ የብቃቱ ማስረጃዎች እንጂ የሕይወት ብስለት ችሎታ መገለጦች አልነበሩም—ዕብ. 6፡1፤ ቆላ. 1፡28-29፤ ፊልጵ. 3፡12-15፦**

ሀ. በተፈጥሮአዊ ችሎታችን እና በሞት እና በትንሣኤ ባለፈ ችሎታ መካከል ያለውን ልዩነት ማየት ያስፈልገናል፤ በእግዚአብሔር ነገሮች የተፈጥሮአዊ ማንነታችንን እና የተፈጥሮአዊ ችሎታችንን አቅመቢስነት፣ አለመብቃት መገንዘብ ያስፈልገናል—ሐዋ. 7፡22፤ ዘጸ. 3፡2-3፣ 14-15፤ 1 ቆሮ. 2፡14፤ ፊልጵ. 3፡3-9፤ 2 ቆሮ. 3፡5-6።

ለ. በእግዚአብሔር ነገሮች በተፈጥሮአዊ ማንነታችን ምንም አይነት መታመን ሊኖረን አይገባም፤ ይልቁንም፣ ተፈጥሮአዊ ማንነታችንን መቃወምን እና ለክርስቶስ አካል ሕይወታዊ ግንባታ በሁሉም ነገር መንፈሳችንን ማንቀሳቀስን መማር አለብን—ፊልጵ. 3፡3፤ ሮሜ 8፡4፤ 1 ጢሞ. 4፡7።

ሐ. በጌታ ምለሳ ለተፈጥሮአዊ ማንነታችን ስፍራ የለም፤ በጌታ ምለሳ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት፣ እንደ ሕያዉ የክርስቶስ አካል ክፍሎች፣ ተፈጥሮአዊ የሆነን ማንኛውንም ነገር ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ ይቃወማሉ—1 ቆሮ. 12፡12-13።

መ. በቤተ ክርስቲያን ግንባታ ውስጥ፣ አንድ ላይ መጋጠም ከመቻላችን በፊት በእኛ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ተፈጥሮአዊ ነገር መሰበር አለበት፤ መገንባት የምንችለው በተፈጥሯዊ ማንነታችን ከተሰበርን በኋላ ብቻ ነው—ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ መዝሙር #837፣ ቁጥር 6 እና 7።

ሠ. ተፈጥሮአዊ ችሎታ ራስን ማዕከል ያደረገ እና ትዕቢተኛ እንድንሆን የሚያደርገን ነው፣ ትምክህትን እና ራስ-ማክበርን ያመጣል፤ በትንሣኤ የሆነ ችሎታ ትዕቢተኛ አይደለም፣ በራሱም አይመካም—ተዛ. ቆላ. 1፡17፣ 18፤ ፊልጵ. 3፡3፤ 2 ቆሮ. 12፡9።

ረ. ተፈጥሮአዊ ችሎታ ራስ ወዳድ ነው፣ ስልቶቹ እና መሣሪያዎቹ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ግድ የሌላቸው ለእኔነት የሆኑ ናቸው፤ በትንሣኤ የሆነ ችሎታ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ ተሰብሯል፣ ለእኔነት አይደለም፣ የእኔነት ንጥረ-ነገርም የለውም—ተዛ. ማቴ. 16፡24።

ሰ. ተፈጥሮአዊ ችሎታ በራሱ በመንቀሳቀስ እና በራሳችን ላይ እንጂ በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ እንዳንሆን በማድረግ በራስ-መደገፍን እና በራስ-መተማመንን ይፈጥራል፤ በትንሣኤ የሆነ ችሎታ ምንም እንኳን የእውነት የሚችል እና ብቃት ያለው ቢሆንም በእግዚአብሔር ላይ ይደገፋል፣ በእኔነት መሠረት ለመንቀሳቀስም አይደፍርም፤ በትንሣኤ የሆነ ችሎታ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ነው፣ በምኞቶቹ መሠረትም ለመንቀሳቀስ አይደፍርም—ተዛ. 2 ቆሮ. 1፡8-9፤ 4፡6-7፤ 12፡7-9።

ሸ. ተፈጥሮአዊ ችሎታ መለኮታዊ ንጥረ-ነገር የለውም፤ የራሱን ክብር ይሻል፣ የራሱን መሻቶችንም ያረካል፤ ከሥጋና ከንዴት ንጥረ-ነገሮች ጋር የተዋሐደ ነው፤ ስለዚህ፣ ተቀባይነት ሳያገኝ ሲቀር፣ ይቆጣል፤ በትንሣኤ የሆነ ችሎታ ሥጋ የለውም—ተዛ. 1 ተሰ. 2፡4።

ቀ. ተፈጥሮአዊ ችሎታ ጊዜያዊ እና ፈተናዎችን፣ እንቅፋቶችንና ተቃውሞዎችን መቋቋም የማይችል ነው፤ በትንሣኤ የሆነ ችሎታ ለአብ ፈቃድ እውቅና በመስጠት አብን ያመሰግናል—ማቴ. 11፡20-26፤ ዮሐ. 2፡19፤ ሐዋ. 2፡24።

በ. በተፈጥሮአዊ ችሎታ መሠረት የሚያገለግሉ ከሌሎች ሽልማቶችን ወይም አድናቆቶችን ይሻሉ፤ በትንሣኤ በሆነ ችሎታ መሠረት የሚያገለግሉ ክርስቶስን ለማግኘት ይሻሉ፣ እርሱን ደስ የሚያሰኝ የመሆንን ክብር ለማግኘትም የቆረጡ ናቸው—ፊልጵ. 3፡8፤ ዘኍ. 15፡1፤ ዕብ. 11፡5-6፤ 2 ቆሮ. 5፡9።

ተ. ተፈጥሮአዊ ችሎታ ራሱን መግለጥ፣ በሰው መታወቅ እና በሰው ፊት መታየት ይወዳል፤ በትንሣኤ የሆነ ችሎታ ራሱን ከሚሰውረው አምላክ ጋር አንድ ለመሆን ነገሮችን በስውር ማድረግን እና ሥሩን ወደ ታች መስደድን፣ ወደ ላይም ማፍራትን ይወዳል—ኢሳ. 45፡15፤ 37፡31፤ ማቴ. 6፡4፣ 6፣ 17-18።

ቸ. ከሕይወት ውጪ ተፈጥሮአዊ ችሎታና ብቃት የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚመርዝ እባብ ናቸው፤ ሕይወት ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሕይወት አቅርቦት እንደሚሰጥና መዓዛ ባላቸው በበለጠጉ ባሕሪያቱ የተትረፈረፈውን አምላክ በሰናይ ባሕሪያቱ በኩል በስብዕናው የሚገልጥ ሰው እንድንሆን እንደሚያደርግ ርግብ ነው፤ ሕይወት ከእሾኽ ውስጥ እንደሚየድግ እንደ የቆላ አበባ እና በጨለማ ሌሊት እንደሚያበራ ብሩህ ኮከብ እንድንሆን ያደርጋል—ተዛ. ዘጸ. 4፡1-9፤ ማቴ. 3፡16-17።

ኀ. ሰዎች ተፈጥሮአዊ ችሎታቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣት በሚሞክሩበት ጊዜ ሁሉ፣ የቤተ ክርስቲያን እውነታ ይጠፋል፤ በሞት እና በትንሣኤ ያለፈ ነገር ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ይችላል—1 ቆሮ 3፡16-17።

IV. **አርባ አንዱ የእስራኤል እና የይሁዳ ነገሥታት ከፍተኛ ሥልጣን ላይ ነበሩ፣ በመልካሚቱ ምድር ድሰታቸው ግን ጠንቃቃ አልነበሩም፤ ዳዊት እንኳን ሳይቀር መልካሚቱን ምድር በሙላት አልተደሰተም፤ የእነርሱን ምሳሌ በራሳችን ላይ መተግበር አለብን፡-**

ሀ. የከፉዎቹ ነገሥታት የክፋት ሥር፣ ልክ እንደ እስራኤል ሕዝብ ክፋት፣ አምላክ የሆነውን እርሱን እንደ ሕያው ውኆች ምንጭ መተዋቸው እና ውኃ እንደማይዙ እንደ ተቀደዱ ጉድጓዶች ወደ አረማዊ ጣዖታት መዞራቸው ነበር፤ እነዚህ ሁለት ክፋቶች በጣዖት አምልኮ እና ሥጋዊ ምኞትን በማርካት ሙት ውኆች ውስጥ አሰጠሚቸው—ኤር. 2፡13።

ለ. ዛሬ የጸጋን እና የጽድቅን ስጦታ ብዛት በመቀበል ከክርስቶስ ጋር እየነገሥን ያለን ነገሥታት ነን (ሮሜ 5፡10፣ 17)፤ ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀለ እና ከዚያ ወዲያ እርሱ እንዳልኖረ እና ክርስቶስ በእርሱ እንደኖረ (ገላ. 2፡20) ማወጅ የቻለውን የጳውሎስን ምሳሌ ለመከተል መትጋት አለብን፤ የተትረፈረፈውን የኢየሱስ ክርስቶስን መንፈስ አቅርቦት፣ የአካሉን አቅርቦት በመቀበል ክርስቶስ ለመጉላቱ ክርስቶስን እንደኖረ ተናግሯል (ፊልጵ. 1፡19-21)።

ሐ. ክርስቶስ በትንሣኤ እንደ የሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ ሆነ (1 ቆሮ. 15፡45)፤ ይህ መለኮታዊ፣ ሁሉን-ያካተተ መንፈስ ወደ መንፈሳችን ይገባና ዳግም ከተወለደው መንፈሳችን ጋር ይዋሐዳል፣ እግዚአብሔር እና ሰው፣ ሰው እና እግዚአብሔር በተዋሐደው መንፈስ አንድ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ሁለቱ መንፈሶች አሁን እንደ አንድ አካል በአንድ ላይ ተዋሕደዋል (6፡17፤ ሮሜ 8፡16)።

መ. ዛሬ እግዚአብሔር መንፈስ ሁሉን-ያካተተ መንፈስ፣ የተቀመመ መንፈስ፣ የሚቀባው መንፈስ፣ የሚገልጠው መንፈስ እና በሂደት እንዳለፈው ሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ የተጠናቀቀው መንፈስ ነው—ፊልጵ. 1፡19፤ ዘጸ. 30፡22-25፤ 1 ዮሐ. 2፡27፤ 1 ቆሮ. 2፡10፤ ራእ. 22፡17።

ሠ. በጌታ ምለሳ ዛሬ፣ የእውነት በሕይወት መንገሥ እንችል ዘንድ ሙሉ ትኩረታችንን በተዋሐደው መንፈስ ላይ፣ ከመንፈሳችን ጋር በተዋሐደው መንፈስ ላይ ማድረግ እና በዚህ በተዋሐደ መንፈስ ውስጥ እና መሠረት መኖር፣ መመላለስ እና ማንነታችንን ማድረግ አለብን (ሮሜ 8፡4፤ 5፡10፣ 17)፤ ይህ የተዋሐደ መንፈስ የክርስቶስ አካል ጅማሬ ነው፣ በአዲሲቱ ኢየሩሴምም ይጠናቀቃል (ኤፌ. 1፡17፤ 2፡22፤ 3፡5፣ 16፤ 4፡23፤ 5፡18፤ 6፡18፤ ራእ. 21፡10)።

*© 2022 Living Stream Ministry*